# ከገዙት 10 ሎቶ ቲኬቶች ......

ከሁለት ወር በፊት አንድ ማህበር ያቋቁማሉ። ይህ ማህበር በ22 ጓደኛሞቹ የተመሰረተ ሲሆን የተቋቋመበት ዓለማም  ማህበሩ ያለፈውን ለማስታወስና የነበረውን ማህበራዊ ሕይወት በጠንካራ መሰረት ለማኖር ነው። ዛሬም 21 ጓደኛሞች ማህበሩ አሰባስቧቸዋል። አዲስ አበባ ምኒሊክ ሆስፒታል አጠገብ ካለው የህዝብ መዝናኛ ሳቅ ደርቷል። አንዲት ጎልማሳ ሴት ነገ የሚወጣ ሎተሪ እያለች አጠጋበቻው ስትደርስ ከተሰበሰቡት መካከል የፈለጉትን ያህል ሎቶ ሎተሪ ይቆርጣሉ።

አቶ መልካሙም ያቺ ጎልማሳ ሴት ከያዘቻው ቲኬቶች በቁጥር 10 ይቆርጣሉ። ምክንያቱም የሴትዮዋ ሁኔታ ሆዳቸውን በልቶ ነበር።ከአስሩ ቲኬት ውስጥ አንዷ የአንደኛው ዕጣ ጃክፖት አሸናፊ እንዲሆኑ የዕድል በር ከፈተች።

ሙሉ ስማቸው መልካሙ ክብረት ሲሆን የሁለት ልጆች አባት ናቸው። የሎተሪ ደንበኝነታቸውም ከ1974 ዓ.ም. ጀምሮ እንደሆነና አንዳንዴም ሎተሪ በዱቤ እንደሚቆርጡ  ተናግረዋል።

አቶ መልካሙ በደረሳቸው ዕድል ምክንያት ጓደኞቻቸው ባዘጋጁት የእንኳን ደስ ያለህ ግብዣ ወዳጅ ዘመድ ደስታውን ሲገልፅ  ተመልክተናል።ደስታቸውን ያከበሩት እዚያው



ከቆረጡበት መዝናኛ ሲሆን ዘመዶቻቸው ላይም ደስታው ተጋብቶ አይተናል። በዚህ ጊዜ ባለቤታቸው አገኘተናቸው እንዲህ አሉን “ቀደምሲል በገንዘብ አስከፋላችሁ የምታስለፈልፉ ይመስለኝ ነበር። እውነት ነው የምልህ ሎተሪው ደረሰኝ ሲለኝ ሰውነቴን ነው ያንቀጠቀጠኝ ከዚህ በኂላ ዳቦ የምበላበትን ሎተሪ ነው የምቆርጥበት” ብለውናል።

አቶ መልካሙ በአዲስ አበባ የሸገር መናፈሻ የውል ማስረጃ ክፍል አስተባበሪ ናቸው። በደረሳቸው ዕድልም እንደ ሰው ሰው ልሆን ነው በማለት ገልጸው በደረሳቸው ብር ቤት ካገኙ እንደሚገዙ ተናግረዋል።